# የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 94/2006

ጥር 2006

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

# <u>የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 94/2006</u>

የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን በአዋጁ ከተደነገጉ መርሆዎችና ዘዴዎች ጋር በማጣጣም ለማስፈፀም በማስፈለጉ፣

የገቢ ዕቃዎች ዋጋ አተማመን በተሻለ ደረጃ ዘመናዊ፣ ግልጽና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በወጥነት ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የባለስልጣኑ የሥራ ክፍሎች፣ ቅ/ጽ/ቤቶች እና የጉምሩክ ኦፊሰሮች ከዋጋ አተማመን ጋር በተያያዘ የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወሰን በማስፈለጉ፣

አስመጪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በዋጋ አተማመን ረገድ የሚኖራቸውን መብትና የተጣለባቸውን ግዴታ ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ፣

ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀጽ 32(4) ስለዋጋ መተመኛ ዘዴዎች እና የዋጋ አተማመን ስርዓት አፈጻጸም በመመሪያ እንዲወሰን እና በአንቀጽ 112(2) የአፈጻጸም መመሪያ እንዲያወጣ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይኸንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ፡</u>

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ "**የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 94/2006**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "ገቢ ዕቃ"፡- ማለት ወደ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የሚገባ ዕቃ ማለት ነው፡፡

2) "የጉምሩክ ዋጋ" ፡- ማለት የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሲሆን በጉምሩክ አዋጅ እና በዚህ መመሪያ በተደነገጉት የዋጋ አተማመን ዘዴዎች አማካኝነት የሚሰላ እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈለ/የሚከፈል ጠቅላላ ወጪ ነው፡፡

3) "የማነፃፀሪያ ዋጋ" ፡- ማለት በአስመጪው/ወኪሉ የቀረበውን የገቢ ዕቃ ዋጋ ትክክለኛነት ለማጣራት እና ለመወሰን የሚያገለግል የገቢ ዕቃዎች ዋጋ ነው፡፡

4) "በአንድ ሀገር የተመረቱ ዕቃዎች" ፦ ማለት በአንድ ሉአላዊት ሀገር የተመረቱ ዕቃዎች ማለት ሲሆን፤ በተፈጥሮ የተገኙ ወይም በቁፋሮ የተገኙ እቃዎችን ይጨምራል፡፡

5) "በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ የሚገኙ አገሮች" ፦ ማለት በአለም አቀፍ የንግድ ድርጅት (WTO) ወይም በተባበሩት መንግስታት (UN) የአገሮች የእድገት ደረጃ ዝርዝር መሰረት በተመሳሳይ ዕድገት ደረጃ የሚገኙ አገራት ሲሆኑ የአህጉራዊ ነባራዊ ሁኔታም ከግንዛቤ የሚያስገባን የአገራት ዝርዝርን ይጨምራል፡፡

6) "ተቀራራቢ ዕቃ" ፦ ማለት በአንድ አይነት ኢንዱስትሪ ወይም በአንድ አይነት የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመረቱ ዕቃዎች ማለት ሲሆን፤ የአንድ ዓይነት እቃዎችና ተመሳሳይ ዕቃዎችን ይጨምራል፡፡

7) "የጉምሩክ ዋጋ ማጣራት" ፦ ማለት በሚመለከታቸው የጉምሩክ ኦፊሰሮች አማካኝነት በአስመጪው/ወኪሉ ዲክሌር የተደረገው የዕቃዎች ዋጋ ትክክለኛ የጉምሩክ ዋጋ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ወይም ለማጣራት ይቻል ዘንድ ለዋጋው ወይም ለስሌቱ መነሻ የሚሆኑ ሰነዶችን የመመርመር ሂደት ሲሆን፤ የመጀመሪያ የዋጋ ማጣራት፣ በድጋሚ የማጣራት እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በትክክል እስከሚሰላ ድረስ የሚደረገውን የዋጋ ማጣራት ሂደት ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

8) "ዋጋ የመወሰን ስልጣን" ማለት አስመጪው/ወኪሉ ከዋጋ ትመና ጋር በተያያዘ ስለፈጸማቸው ጥፋቶች ወይም ልዩነት ስለመገኘታቸው በዋጋ አጣሪ ኦፊሰሮች አማካኝነት ዋጋ የማጣራት፣የማስተካከል ወይም ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት ሂደት ነው፡፡

9) "የጉምሩክ ዋጋ ውሳኔ ክለሳ" ፦ ማለት በሥራ ኃላፊነት መሠረት በአንድ ኦፊሰር የተሰጠ የዋጋ ትመና ውሳኔ በስራ ላይ ካላው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አንጻር ስላለው ትክክለኛነት ቢያንስ በአንድ ደረጃ በበላይ ኦፊሰሮች ወይም በክለሳ ኮሚቴ አማካኝነት የሚተገበር በድጋሚ የማጣራት ሂደት ነው፡፡

10) "የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን (Valuation Details Declaration)" ፦ ማለት የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን የሚያስፈልጉ መግለጫዎችና መረጃዎችን አስመጪው/ወኪሉ በመሙላት ለባለስልጣኑ በዝርዝር የሚያሳውቅበት በባለሥልጣኑ የተዘረጋ ሥርዓት ወይም የተዘጋጀ የኤሌክትሮኒክ መረጃ ማሳወቂያ ሥነ-ሥርዓት ሲሆን፤ በወረቀት መልክ የሚዘጋጅ ቅጽንም ይጨምራል፡፡

11) “የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት” ፡- ማለት በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኙ የገቢ እቃዎች ዋጋ መረጃን እና የአለማቀፍ ዕቃዎች ዋጋ መረጃን መሠረት በማድረግ የሚደራጅ ለዋጋ ማነጻጸሪያነት የሚያገለግል የመረጃ ዳታቤዝ ነው፡፡

12) “ዳይሬክቶሬት” ፡- ማለት የዋጋ ትመና እና የታሪፍ ምደባ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

13) “ቅ/ጽ/ቤት”፡-ማለት የጉምሩክ ስነስርአት የሚፈጸምባቸው የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡

14) “ባለሥልጣን” ፡- ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

15) “አዋጅ” ፡- ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

16) በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላት እና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በሚገቡ ገቢ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ስለ ጉምሩክ ዋጋ አወሳሰን ሁኔታ</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>
### <u>የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ዘዴዎች አፈፃፀም</u>

4. <u>መርህ</u>

የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ዋጋ በሚወሰንበት ወቅት በአዋጁ ከአንቀጽ 32 እስከ 44 የተመለከቱትን የግብይት ዋጋ፣ የአንድ አይነት ዕቃዎች ዋጋ ፣ የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ ፣ ወደ ኂላ የማስላት ዘዴ ፣ በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ ዘዴ እና ሚዛናዊ የዋጋ አተማመን ዘዴዎችን በቅደም ተከተል በመጠቀም ይሆናል፡፡

5. <u>የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ አፈፃፀም</u>

1) ወደአገር ውስጥ ለሚገባ እቃ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ለእቃው በትክክል የተከፈለው ወይም የሚከፈለው የግብይት ዋጋ ሲሆን በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች ታክለውበት ነው፡፡

2) በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በአስመጪው የቀረበው የግብይት ዋጋ በቀጥታ ተቀባይነት የማይኖረው ወይም ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 33(1)(ሀ)-(መ) የተቀመጡት መስፈርቶች ካልተሟሉ እና የዋጋ ትመና ኦፊሰሩ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንዱ አለ ብሎ ሲያምን ወይም ሲገምት ነው፡-

ሀ. በዋጋ ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የዕቃው መግለጫዎች ፣ የጥራት፣ የብዛት፣ የምርት-ሀገር፣ የምርት ዘመን መግለጫዎች እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ማስረጃዎች በትክክል ካልተገለጹ ወይም ካልቀረቡ፣

ለ. በሀሰት የተዘጋጀ ወይም የተጭበረበረ ሰነድ ወይም ማስረጃ ከቀረበ፣

ሐ. በአዋጁ አንቀፅ 39 ላይ የተጠቀሱት ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የግብይት ዋጋ ውስጥ ካልተካተቱ ወይም ዋጋቸውን ለመተመን የሚያስችሉ ተጨባጭ ማስረጃዎችን አስመጪው ካላቀረበ፣

መ. በአስመጪው የቀረበው የዕቃው ዋጋ እና በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታቤዝ ውስጥ የሚገኙ የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች አማካይ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ከ10% በላይ ከሆነ፣

ሠ. በአስመጪው የቀረበው የዕቃው ዋጋ በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች ከተሸጠ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች በወደኋላ ማስላት ዘዴ መሰረት ተቀባይነት ያገኘ አማካይ የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ ከ10% በላይ ከሆነ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲከሰቱ፡-

ሀ. የዋጋ ትመና ኦፊሰሩ የአስመጪውን ዋጋ የጠረጠረበትን ምክንያት በመግለጽ አስመጪው በአካል ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም ስለ ዕቃው ዋጋ ትክክለኛነት የሚያስረዱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ በጽሁፍ ይጠይቃል፣

ለ. አስመጪው ማስረጃ እንዲያቀርብ ከተገለጸለት ቀን አንስቶ በ15 (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ማስረጃዎቹን ማቅረብ አለበት፣

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2(መ) እና (ሠ) የተመለከተው ሲያጋጥም በአስመጪው የቀረበው የዕቃው ዋጋ ተቀባይነት የሚኖረው ዋጋው ሌሎች አስመጪዎች ከገዙበት ተቀራራቢና ትክክለኛ የዕቃው ዋጋ መሆኑን ወይም በዓለማቀፍ ደረጃ የታወቀ የዋጋ ለውጥ መኖሩን በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ለባለስልጣኑ ማስረዳት ከቻለ እና በሚለመለከተው የቅ/ጽ/ቤት የሥራ አስኪያጅ ወይም በዳይሬክቶሬቱ ደረጃ ሲፈቀድ ነው፡፡

መ. አስመጪው ማስረጃዎቹን ካላቀረበ ወይም ያቀረበው ማስረጃ የዋጋ ትመና ኦፊሰሩን ጥርጣሬ ሊያስወግድ ካልቻለ የዋጋ ትመና ኦፊሰሩ ጥርጣሬውን ያላስወገደበትን ምክንያት በግልጽ በማስቀመጥ እና ለአስመጪው በጽሑፍ በማሳወቅ ወደሚቀጥለው የዋጋ አተማመን ዘዴ ይሸጋገራል፡፡

## 6. ግኑኝነት ያላቸው አካላት ዋጋ ተቀባይነት ስለሚያገኝበት ሁኔታ

1) በገዢና ሻጭ መካከል ግኑኝነት ሲኖር በባለስልጣኑ የሚዘጋጀውን መጠይቅ ወይም/እና ቅጽ አስመጪው በአግባቡ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፣

2) በአዋጁ በአንቀጽ 33 መሠረት ግኑኝነት ባላቸው ሰዎች መካከል በተደረገ ግብይት የቀረበው የዕቃው ዋጋ ተቀባይነት የሚኖረው ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፣

ሀ. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ያለመኖራቸውን የዋጋ ትመና ኦፊሰሩ ካረጋገጠ፣

ለ. አስመጪው በገዢና ሻጭ መካከል ያለው ግኑኝነት በዋጋው ላይ ተጽዕኖ ያላሳደረ መሆኑን በተጨባጭ ማስረጃዎች ለባለስልጣኑ ማስረዳት ከቻለ፣

ሐ. አስመጪው በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጠ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ ከ10% የበለጠ ከሆነ አስመጪው ያቀረበው ዋጋ ሌሎች አስመጪዎች ከገዙበት ተቀራራቢ እና ትክክለኛ መሆኑን በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ማስረዳት ከቻለ፣

መ. ቅ/ጽ/ቤቱ በማንኛውም ሌላ ዘዴ ተጠቅሞ ወይም ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ የተወሰነ የዕቃ ዋጋ ጋር ያለው ልዩነት ከ10% ያልበለጠ ከሆነ ፣

ሠ. አስመጪው በተመሳሳይ ወቅት በወደ ኋላ በማስላት ወይም በወጪ ስሌት ዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት የተወሰነ የዕቃ ዋጋ ጋር ያለው ልዩነት ከ10% የበለጠ ከሆነ አስመጪው ያቀረበው ዋጋ ሌሎች አስመጪዎች ከገዙበት ተቀራራቢ እና ትክክለኛ መሆኑን በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ማስረዳት ከቻለ፣

## 7. ግኑኝነት አለ ተብሎ በሚጠረጠርበት ጊዜ ስለሚኖር አሰራር

1) ቅ/ጽ/ቤቱ አስመጪው ከሻጭ ጋር ግንኙነት አለው ብሎ ከጠረጠረ ወይም ውሳኔ መስጠት ካልቻለ ተገቢውን ዋስትና በመያዝ ለጊዜው በማስተናገድ ቀጣይ ማጣራት እንዲደረግ ዝርዝር

ሪፖርት ከአስፈላጊው ደጋፊ ሠነዶችና ማስረጃዎች ጋር በአምስት ቀናት ውስጥ ለዳይሬክቶሬቱ መላክ አለበት፣

2) ዳይሬክቶሬቱ ከቅ/ጽ/ቤት የተላከውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ በአዋጁ በተደነገገው መሰረት ግኑኝነት ያላቸው መሆኑ ወይም አለመሆኑን በማጣራትና በማረጋገጥ የደረሰበትን ውጤት ለሚመለከተው ቅ/ጽ/ቤት በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ያሳውቃል፣

3) ቅ/ጽ/ቤቱም ከዳይሬክቶሬቱ የተላከው ውጤት እንደደረሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች አስመጪው ከሚያቀርበው መረጃ በመነሳት በማጣራት በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ማሳወቅ አለበት፡-

    ሀ. የዕቃው ዋጋ የተወሰነበት ሁኔታ በተለይ ዕቃውን በሚያመርተው የኢንዱስትሪ ዘርፍ በማንኛውም ነፃ የውድድር ገበያ ሁኔታ ትክክለኛ ዋጋ በሚወሰንበት ሁኔታ የተወሰነ መሆኑን፣

    ለ. ዋጋው የተወሰነው ከሻጩ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሌሎች ገዢዎች በተወሰነበት ሁኔታ መሆኑን፣

    ሐ. የግብይት ዋጋው አጠቃላይ ዕቃውን ለማምረት የሚያስወጣውን ወጪ እና አምራቹ በተመሳሳይ ወቅት ተመሳሳይ ዕቃ በመሸጥ ከሚያገኘው ትርፍ ጋር የሚመጣጠን ትርፍ ሊያስገኝ የሚችል መሆኑን ናቸው፡፡

4) ግኑኝነት ያላቸው አካላት ያቀረቡት የዕቃ ዋጋ(የኢንቮይስ ዋጋ) ቅ/ፅ/ቤቱ ካልተቀበለ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለአስመጭው በመግለፅ የሚቀጥለውን የዋጋ አተማመን ዘዴ ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

## 8. <u>የአንድ አይነት ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን ዘዴ አፈጻጸም፡</u>

1) የዕቃውን ዋጋ በግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ መወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀጽ 34 በተደነገገው መሠረት ዕቃው ከመግባቱ በፊት በነበሩት 90 ቀናት ውስጥ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃ እና በተቀራራቢ ብዛት ወደ ሀገር ገብተው በነበሩና ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጡ የአንድ አይነት ዕቃዎች አስመልክቶ አስመጪው በሚያቀርበው የዋጋ መረጃ በመነሳት የዋጋ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

2) ከላይ በንኡስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሰረት አስመጪው ከሚያቀርበው መረጃ በመነሳት ቅ/ጽ/ቤቱ የዋጋ ውሳኔ ሲያስተላልፍ በአስመጪ የሚቀርበውን መረጃ በማጣራት እና የተሟላ በማድረግ ሂደት የሌሎችን አስመጪዎች መረጃ ሚስጢራዊነት በመጠበቅ ሊጠቀም ይገባል፣

3) የአንድ አይነት ዕቃዎች ዋጋ በባለሥልጣኑ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት ከሚገኘው የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋን በማነፃፀር የሚወስን ሆኖ፣

ሀ. ሁለትና ከዚያ በላይ የአንድ አይነት ዕቃ ማነፃፀሪያ ዋጋ በሚገኝበት ወቅት የጉምሩክ ዋጋ ማነፃፀሪያ ተደርጎ የሚወሰደው አማካኙ ዋጋ ይሆናል፣

ለ. አስመጪው ዲክሌር ያደረገው የዕቃው ዋጋ በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች ከተሸጠ የአንድ ዓይነት ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ ከ10% የበለጠ ቢሆንም ያቀረበው ዋጋ ሌሎች አስመጪዎች ከገዙበት ተቀራራቢ እና ትክክለኛ የዕቃው ዋጋ መሆኑን ወይም በዓለማቀፍ ደረጃ የታወቀ የዋጋ ለውጥ መኖሩን በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ለባለስልጣኑ ማስረዳት ከቻለ እና በሚለመለከተው የቅ/ጽ/ቤት የሥራ ሀላፊ ወይም በዳይሬክቶሬቱ ደረጃ ሲፈቀድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

9. <u>የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን ዘዴ አፈጻጸም :</u>

1) የዕቃው ዋጋ በአንድ ዓይነት ዕቃ ዋጋ አተማመን ዘዴ ሊወሰን ካልተቻለ በአዋጁ በአንቀጽ 35 በተደነገገው መሠረት አስመጪው ዲክሌር ያደረገው ዕቃ ከመግባቱ በፊት በነበሩት 90 ቀናት ውስጥ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃ እና በተቀራራቢ ብዛት ወደ ሀገር ገብተው በነበሩ ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጡ የተመሳሳይ ዕቃዎችን አስመልክቶ አስመጪው በሚያቀርበው የዋጋ መረጃ በመነሳት የዋጋ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

2) ከላይ በንኡስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሰረት አስመጪው ከሚያቀርበው መረጃ በመነሳት ቅ/ጽ/ቤቱ የዋጋ ውሳኔ ሲያስተላልፍ በአስመጪ የሚቀርበውን መረጃ በማጣራት እና የተሟላ በማድረግ ሂደት የሌሎችን አስመጪዎች መረጃ ሚስጢራዊነት በመጠበቅ ሊጠቀም ይገባል፣

3) የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ በባለሥልጣኑ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት ከሚገኘው የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ በማነፃፀር የሚወሰን ሆኖ፡-

ሀ. ሁለትና ከዚያ በላይ የተመሳሳይ ዕቃ ማነፃፀሪያ ዋጋ በሚገኝበት ወቅት የጉምሩክ ዋጋ ማነፃፀሪያ ተደርጎ የሚወሰደው አማካኙ ዋጋ ይሆናል፣

ለ. አስመጪው ዲክሌር ያደረገው የዕቃው ዋጋ አስመጪው በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጠ የተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ ከ10% የበለጠ ቢሆንም ያቀረበው ዋጋ ሌሎች አስመጪዎች ከገዙበት ተቀራራቢና ትክክለኛ መሆኑን ወይም በዓለማቀፍ ደረጃ የታወቀ የዋጋ ለውጥ መኖሩ በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ለባለስልጣኑ ማስረዳት ከቻለ እና በሚለመለከተው የቅ/ጽ/ቤት የሥራ ሀላፊ ወይም በዳይሬክቶሬቱ ደረጃ ሲፈቀድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

10. <u>ወደ ኋላ የማስላት ዘዴ አፈጻጸም፡</u>

1) በአዋጁ በአንቀጽ 36 በተደነገገው መሠረት የዕቃዎችን ዋጋ ለማስላት ግንኙነት በሌላቸው ገዢና ሻጭ መካከል በተደረገ ግብይት በአስመጪው ወይም በሌሎች አስመጪዎች እቃው ከተጫነበት አገር በቀጥታ ወይም ከሌላ አገር ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ፣ ወይም የገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በከፍተኛ ብዛት በሀገር ውስጥ በተሸጡበት ነጠላ ዋጋ ላይ በመመስረት ይወሰናል።

2) በዚህ አንቀጽ በተደነገገው ዘዴ መሠረት የጉምሩክ ዋጋ ሊተመን የሚችለው፡-

ሀ. ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል ሻጩ ማለት አስመጪው ሲሆን ገዥው ማለት ዕቃውን ከአስመጪው የገዛ እንደሁኔታው አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ወይም የመጨረሻ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ለ. በአዋጁ በአንቀጽ 33 በተደነገገው መሰረት በሻጩ (አስመጪው) እና በገዢው መካከል ግንኙነት ከሌለ ወይም ግንኙነቱ በሽያጭ ዋጋው ላይ ተጽዕኖ እንዳላሳደረ አስመጪው ማስረጃ ማቅርብ ከቻለ፣ እና

ሐ. በገዢ በኩል ለሻጩ ከእቃው ጋር በተያያዘ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ በነፃ ወይም በቅናሽ ዋጋ የተከፈለ ክፍያ ወይም የተሰጠ ስጦታ ከሌላ ነው።

11. <u>በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ የዋጋ አተማመን ዘዴ አፈጻጸም :</u>

1) የዕቃዎች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 37 በተደነገገው መሠረት ለማስላት በዕቃው ዋጋ የሚካተቱ ለዕቃው የተከፈሉ ወይም የሚከፈሉ ክፍያዎችና ወጪዎችን ከአምራቹ ድርጅት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚገኙት መረጃዎች እና ደጋፊ ማስረጃዎች በመመርኮዝ ሊወሰን ይችላል፣

2) በአዋጁ አንቀጽ 37 ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ በላኪው ሀገር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ ወይም በዕቃው ንግድ ዘርፉ አብዛኛውን ጊዜ ያለው የተለመደ ወይም አማካይ የመሸጫ፣ የማሸጊያና ሌሎች ወጪዎች እና የትርፍ መጠን ማስረጃ ላይ በመመርኮዝ ሊወስን ይችላል።

12. <u>ሚዛናዊ የዋጋ አተማመን ዘዴ አፈጻጸም</u>

የዕቃዎች ዋጋ በአዋጁ በአንቀጽ 37 በተደነገገው የዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 8 እስከ 11 የተጠቀሱትን የዋጋ ትመና ዘዴዎችን በቅደም ተከታላቸው አተረጓጎማቸውን በማስፋት በአዋጁ ከተደነገገው አጠቃላይ መርህ ጋር የተጣጣመ ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ወቅታዊ መረጃ መሰረት ከዚህ በታች በተገለጸው አግባብ በቅደም ተከተል ዋጋ ይወሰናል።

1) **የአንድ አይነት ዕቃ ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ሚዛናዊ ዘዴ፡-**

ሀ. በ90 ቀናት ውስጥ የገባ የአንድ አይነት ዕቃ ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ በማይገኝበት ወቅት በ180 ቀናት ወደ ሀገር የገባ የአንድ አይነት ዕቃ ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ እንደ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ለ. ከገቢ ዕቃው ጋር በአንድ ሀገር የተመረተ አንድ አይነት ዕቃ ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ በማይገኝበት ወቅት በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ በሚገኝ አገር የተመረተ አንድ አይነት ዕቃ ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ እንደ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ሐ. ወደኋላ በማስላት እና በወጪ ስሌት ላይ በተመሰረተ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት የተወሰኑ የአንድ አይነት ዕቃ ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

2) **ወደ ኋላ ማስላት ሚዛናዊ ዘዴ፡-**

ሀ. በብዛት የተሸጠበት ዋጋ ካልተገኘ በነጠላ የተሸጠበትን ዋጋ የጉምሩክን ዋጋ ለማስላት እንደመነሻ መውሰድ ይቻላል፣

ለ. ባለሥልጣኑ በተጨባጭና ሊለኩ የሚችሉ መረጃዎች ማግኘት በማይችልበት ጊዜ ለአሠራር በሚመች መልኩ ሚዛናዊ መረጃ ወይም ቀመር/ፎርሙላ በመጠቀም ሊወስን ይችላል፡፡

ሐ. ባለሥልጣኑ ሚዛናዊ ቀመሩን/ፎርሙላውን/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኦፕሬሽን ዲዛይን ፕሮግራምና ልማት ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር በኩል ሰርኩላር ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

3) **በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ በከፊል ላልተገኙ ዕቃዎች የዋጋ አወሳሰን ሁኔታ፡-**

ሀ. ባለሥልጣኑ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው የገቢ እቃዎች ዋጋን በተመለከተ በአስመጪው የቀረበው የዋጋ ዝርዝር በከፊል በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ በማይገኝበት ጊዜ፣ በዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ ዋጋ ተገኝቶላቸው ሆኖም በማሳነስ የቀረቡት እቃዎች ዝርዝር ነጠላ ዋጋ (የዳታ ዋጋ) ድምር ሲካፈል በአስመጪው በማሳነስ የቀረቡት ዝርዝር የዕቃዎች ነጠላ ዋጋ(የኢንቮይስ ዋጋ) ድምር በማስላት በሚገኘው አማካኝ ልዩነት ውጤት (ሬሾ) በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ ዋጋ ያልተገኘላቸው ዝርዝር ዕቃዎች ነጠላ ዋጋ በማባዛት ማስተካከል ወይም ማሻሻል(Uplift ማድረግ) ይቻላል፡፡

ለ. በዚህ ንኡስ አንቀጽ መሠረት የሚከናወነው የዋጋ አወሳሰን ተፈጻሚ የሚሆነው ቅ/ጽ/ቤቱ ሁሉንም የዋጋ አተማመን ዘዴዎች ሙከራ በማድረግ ውሳኔ መስጠት በማይችልበት ጊዜ ሲሆን፣ አግባብነት ያለውን የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ይጠቀማል፡፡

ሐ. በዚህ ንኡስ አንቀጽ መሠረት የዋጋ ማስተካከያ ሲደረግ፣ በማሳነስ ከቀረበው ዝርዝር አግባብነት ያለው ናሙና ለማስተካከያነት በሚወሰድበት ጊዜ የተሰጠው ውሳኔ ዋጋው ተመጣጣኝ መሆኑ ለማረጋገጥ የእቃውን ብዛት፣ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ እቃ ወይም በአንድ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመረቱን እቃዎች ግምት ውስጥ አስገብቶ ነው ፡፡

መ. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3(ሀ) በተገለፀው መሠረት የዋጋ ማስተካከያ ሲደረግ ለማስተካከያነት የሚወሰደው የናሙና መጠን በአስመጪው ከቀረበው ዝርዝር ከ10% (አስር በመቶ) ማነስ የለበትም፡፡

4) **ከድብልቅ ማቴሪያሎች የተሰሩ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን፡-**

ሀ. በአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ መሰረት የሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች ከድብልቅ ማቴርያል የተሰሩ ሲሆን ከድብልቅ ማቴሪያሉ ወስጥ አብዛኛውን እጅ ወይም መቶኛ ወይም መጠን በያዘውና የዕቃውን ትክክለኛ ባህሪ በሚሰጠው ማቴሪያል ላይ በመመስረት ዋጋው ይወሰናል፣

ለ. የድብልቅ ማቴሪያሉ እኩል ሆኖ ሲገኝ ከፍተኛ ዋጋ ባለው ማቴሪያል ዋጋ ላይ በመመስረት ዋጋው ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ስለሚጨመሩ፣ ስለሚቀነሱ እና የማይካተቱ ክፍያዎችና ወጪዎች አጠቃላይ አፈጻጸም ሂደት

### 13. ስለተጨማሪ ክፍያዎችና ወጪዎች አፈጻጸም መሠረት

በአዋጁ አንቀጽ 39 በተደነገገው መሠረት እቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ ለዕቃው የተከፈሉ ወይም የሚከፈሉ ወጪዎችና ክፍያዎች በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መካተት አለባቸው፡፡

14. <u>ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የግብይት ዋጋ ውስጥ የሚካተቱበት ሁኔታ፣</u>

1) በአዋጁ አንቀጽ 39 በተደነገገው መሠረት ተጨማሪ ወጪዎችና ክፍያዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ይካተታሉ፡-

ሀ. በኢንቮይሱ እና ሌሎች የንግድ ሰነዶች ላይ በግልጽ የተካተቱ ስለመሆናቸው ያልተገለጸ ከሆነ፣ ወይም

ለ. የተከፈለውም ዋጋ በትክክል ያልተቀመጠ ከሆነ፣ ወይም

ሐ. ወደ ሀገር ከገባው ዋጋ ሊተመንበት ከቀረበው ዕቃ ጋር በተያያዘ የተከፈሉ ሲሆኑ፤ ወይም

መ. ስለመከፈላቸው ግልጽ መረጃ የቀረበላቸው ከሆነ ነው።

2) በዚህ መመሪያ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ ሲካተቱ፡-

ሀ. እቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈሉት ወይም የሚከፈሉት ወጪዎችና ክፍያዎች በአስመጪው እንዲቀርብ ተደርጎ ወጪው በዚያው መሠረት እንዲካተት ይደረጋል፤

ለ. በአስመጪው የቀረበው የወጪ/ክፍያ ስሌት ተቀባይነት ካላገኘ ወይም በተለያየ አሳማኝ በሆነ ምክንያት መቅረብ ካልቻለ በተመሳሰይ ወቅት ከተመሳሳይ ሀገር በገባ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ለማጓጓዣ የተከፈለ ወጪ መሠረት ይወሰናል፣

ሐ. አስመጪው ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በሌላ አስመጪ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ የአንድ አይነት ወይም ለተመሳሳይ ዕቃ የተከፈለ ወጪ ካቀረበ በዚያ መሠረት ሊወሰንለት ይችላል።

መ. ለዕቃው የሚከፈለው የሮያሊቲ ክፍያ ሊሣላ የሚችለው ዕቃው ወደ ሀገር ከገባ በኋላ በሚሆን ጊዜ የመጨረሻ የዋጋ ውሳኔ ዕቃው ወደ ሀገር እስኪገባ ሊዘገይ ይችላል።

ሠ. የሮያሊቲ ክፍያው በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ ተጠቃሎ በአንድ ጊዜ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ የሚከፈል ከሆነ አስመጪውና ላኪው ያደረጉትን ስምምነት መሠረት ባደረገ መልኩ የቅ/ጽ/ቤቱ የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ክፍል ከአስመጪው ጋር በመነጋገር ተጨባጭ መረጃና ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ሚዛናዊ ውሳኔ ያስተላልፋል።

3) በዚህ መመሪያ ከላይ በተደነገገው መሠረት ተጨማሪ ክፍያዎቹ በተጨባጭ መረጃና ማስረጃ ሊተመኑ ካልቻሉ በአዋጁ በአንቀጽ 39/1/ በተደነገገው መሠረት በሚከተሉት ሁኔታዎች በማስላት በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይካተታሉ፡-

ሀ. ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፓርት ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ፎብ ዋጋ ላይ 5% (አምስት በመቶ) በመጨመር በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል።

ለ. ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያ ወጪዎችና ክፍያዎች ዲክሌር በተደረገው የእቃው ፎብ ዋጋ ላይ የ5% (አምስት በመቶ) በመጨመር በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል፡፡

ሐ. ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የኢንሹራንስ ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ፎብ ዋጋ ላይ የ2% (ሁለት በመቶ) በመጨመር በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል፡፡

4) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የሚጨመሩ ክፍያዎች በተጨባጭና ሊለካ በሚችለው መረጃ ሊተመኑ ካልቻሉ፡-

ሀ. ባለሥልጣኑ ስለ ወጪዎችና ክፍያዎች በተመለከተ ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግል መ/ቤቶች በሚገኙት ታማኝ መረጃዎች መሰረት ሊተምን ይችላል ወይም፣

ለ. ባለሥልጣኑ በአዋጁና በዚህ መመሪያ ጋር በሚጣጣም መልኩ በኦፕሬሽን ዲዛይን ፕሮግራምና ልማት ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር በሚያወጣው ቀመር/ፎርሙላ መሠረት ይወሰናል፡፡

15. <u>በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ የማይካተቱ ክፍያዎች</u>

በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ የማይካተቱ ክፍያዎች በተመለከተ በአዋጁ በአንቀጽ 40 በተደነገው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

16. <u>ግብይት ዋጋ ላይ ስለሚቀነሱ ሂሳቦች</u>

ከግብይት ዋጋ ላይ ስለሚቀነሱ ሂሳቦች በተመለከተ በአዋጅ በአንቀጽ 41 በተደነገገው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እና ዕቃዎች የዋጋ አተማመን ሁኔታ</u>

17. <u>ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እና ዕቃዎች የዋጋ አተማመን ዘዴ</u>

1) ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወይም ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ማስከፋያ ዋጋ (ሲ.አይ.ኤፍ) በሚተመንበት ወቅት በዋናነት ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ሲሆን የአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የአዲስ ተሽከርካሪዎች ፎብ ዋጋ ወይም የአዲስ ዕቃዎች ፎብ ዋጋ

በመውሰድ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ተገቢውን የእርጅና ቅናሽ በማድረግ እንዲሁም ተገቢው ተጨማሪ ወጪዎችንና ክፍያዎችን በመደመር ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ለማድረግ አስመጪው/ወኪሉ ተሽከርካሪውን ወይም ዕቃውን ያገለገለ ስለመሆኑ እና ሌሎች ለዋጋ ትመና አስፈላጊ የሆኑ የዕቃው መግለጫ፣ መረጃዎችና ማስረጃዎችን ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

3) ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እና ዕቃዎች ዋጋ በሚተመንበት ወቅት ከአገልግሎት በኋላ ከኢትዮጵያ ውጭ ለተጨመሩ ዕቃዎች ወይም ለተደረጉ እድሳት የተከፈሉ ወጪዎችና ክፍያዎች ካሉ በተጨባጭ መረጃ እና ማስረጃ በመመስረት በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መካተት አለባቸው፡፡

18. <u>***ያገለገለ ተሽከርካሪ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መሠረት***</u>

1) የእርጅና ቅናሽን ተፈፃሚ ለማድረግ ያገለገለ የተሽከርካሪ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መሠረት ተደርጎ የሚወሰደው፡-

ሀ. ከሌሎች የአንድ ዓይነት/ተመሳሳይ ዕቃዎች መለያ መስፈርቶች( ለምሳሌ የአንድ ሀገር ምርት መስፈርት) በተጨማሪ በምርት ዘመን፣ በሞዴል እና በሞተር ጉልበት ወይም በሲሊንደር አቅም(ሲ.ሲ) መሠረት በባለሥልጣኑ የጉምሩክ የዋጋ ማነፃፀሪያ ዳታቤዝ ውስጥ ከሚገኘው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ጋር በማነፃፀር ይወሰናል፡፡

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) የማነፃፀሪያ ዋጋ ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ በሞዴል ዓይነት ቢለይም በተመሳሳይ የአገለገለ ተሽከርካሪ የምርት ዘመን እና የሞተር ጉልበት መሠረት ይወሰናል፡፡

2 ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. ያገለገሉ የፒክአፕ ፣ የሚኒባስ ፣ የአውቶብስ ወይም የጭነት ተሽከርካሪዎች የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሞዴል፣ የምርት ዘመን እና የመጫን አቅምን ከግምት በማስገባትና(በሰው ብዛት ወይም በኩንታል ወይም በኪሎ ግራም) በማገናዘብ ይወሰናል፡፡

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) ላይ የተመለከተውን መረጃ ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ በሞዴል ዓይነት ቢለይም በተመሳሳይ ተሽከርካሪ የምርት ዘመን እና የመጫን አቅም መሠረት ይወሰናል፡፡

ሐ. ያገለገለ የተሳቢ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በርዝመት፣ በመጫን አቅም፣ በአክስል ብዛትና በምርት ዘመን መሰረት ይወሰናል፡፡

## 19. የእርጅና ቅናሽ አደራረግ ሥርዓት

ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እና ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ በሚሰላበት ጊዜ የሚከተሉትን የእርጅና ቅናሽ አደራረግ ሥርአት ይከተላል፡-

1) ለአገለገሉ ተሽከርካሪዎች የሚደረገው ከታች በተገለፀው ሠንጠረዥ አንድ መሠረት የእርጅና ቅናሽ ከተሽከርካሪው የምርት ዘመን በመነሳት እስከ ሦስተኛው ዓመት መጨረሻ ድረስ ከፎብ/Free on Board or FOB/ ዋጋው ላይ በየዓመቱ የሚደረግ የ10% ቅናሽ ሲሆን ከ30% አይበልጥም፡፡

**ሠንጠረዥ አንድ፡-** **ለአገለገሉ ተሽከርካሪዎች የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ በመቶኛ**

| ተ.ቁ | ተሽከርካሪው ከተመረተበት ቀን ጀምሮ የቆየበት የአገልግሎት ዘመን | የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ መጠን በመቶኛ (ከፎብ ዋጋ ላይ) |
|---|---|---|
| 1 | ከአንድ ዓመት በታች<br>**(ዓመት < 1 )** | 0% |
| 2 | አንድ ዓመት እና ከሁለት ዓመት በታች<br>**(1 ≤ ዓመት <2)** | 10% |
| 3 | ሁለት ዓመት እና ከሦስት ዓመት በታች<br>**(2 ≤ ዓመት < 3)** | 20% |
| 4 | ሦስት ዓመት እና ከ3 ዓመት በላይ<br>**(3 ≥ዓመት)** | 30% |

2) በአስመጪው/ወኪሉ ዲክሌር የተደረገው ገቢ እቃ ከአገለገሉ ተሽከርካሪዎች ውጭ ሌላ ያገለገለ ዕቃ ከሆነ ከእቃው የምርት ዘመን በመነሳት ከአንድ ዓመት በላይ ያገለገለ መሆኑ ሲረጋገጥ ከፎብ ዋጋው ላይ የ30% የእርጅና ቅናሽ በማድረግ እና የቀረበውን ሰነድ (ኢንቮይስ ዋጋ) በማገናዘብ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

3) ከላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማነፃፀሪነት የሚወሰደው ዋጋ ያገለገለ ዕቃ ላይ የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ ከአንድ ዓይነት ወይም ከተመሳሳይ አዲስ ዕቃ ከፎብ ዋጋው ላይ የሚደረግ የ30% ቅናሽ ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች እና ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ ምንም አይነት አገልግሎት ወይም ጥቅም ላይ ሳይውሉ ከአንድ አመት በላይ የቆዩ ቢሆኑም የእርጅና ቅናሽ ሳይደረግባቸው አዲስ በነበሩበት ጊዜ ያለው ዋጋ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት እና የመነሻ ዋጋ የሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች ማደራጀት

### 20. የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት አደረጃጀትና አጠቃቀም

1) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የባለሥልጣኑ ኦፊሰር በአስመጪ/ወኪሉ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች ዋጋቸው ትክክለኛ የግብይት ዋጋ ስለመሆኑ ለማጣራት እና ተገቢውን የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ በአዋጁ መሰረት ለመወሰን የተዘጋጀውን የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት ሲስተም (Ethiopian Customs Valuation System[ECVS]) ይጠቀማል፡፡

2) የዋጋ መረጃ ቋቱ በዋጋ ማጣራት ሂደት፣ በዋጋ ውሳኔ ክለሳ ሂደት፣ በድህረ-እቃ አወጣጥ ኦዲት ጊዜ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የባለሥልጣኑ ሥራዎች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

3) ባለሥልጣኑ በዋጋ መረጃ ዳታቤዝ የሚገኙ መረጃዎችን የአስመጪዎችን/ላኪዎችን ምስጢር በጠበቀ ሁኔታ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እና ሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ጋር የመረጃ ልውውጥ ሊያደረግ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ዳይሬክቶሬቱ ለገቢ ዕቃዎች ዋጋቸውን ትክክለኛ የግብይት ዋጋ ስለመሆናቸው ለማጣራት ለሁሉም ወይም ለተወሰኑ ዕቃዎች በስጋት ሥራ አመራር መሠረት ተቀባይነት ያለው የዋጋ ልዩነት (*permissible Deviations)* ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

5) የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ በመግባት የማየት፣ የመፈተሽ፣ የመጠቀም፣ የማስተካከል እና ሌሎች ሥራዎች ማከናወን የሚቻለው በሚመለከተው የባለስልጣኑ ሰራተኛ ብቻ ሲሆን፤ በሚመለከተው የባለስልጣኑ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ወይም የሥራ ክፍሉ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም የሥራ ኂላፊ ሲፈቀድ እና በመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ሲሰጥ ነው፡፡

6) ማንኛውም የሚመለከተው የባለሥልጣኑ ሠራተኛ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋቱን በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ለሚፈለገው አላማ ብቻ መጠቀም አለበት፡፡

### 21. የመነሻ ዋጋ ስለሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች

1) በዚህ መመሪያ የተደነገገው ቢኖርም የጉምሩክ ዋጋን ወይም የኢንቮይስ ዋጋን አሳንሶ የማቅረብ ድርጊትን ለመከላከል ሲባል ተደጋጋሚ ችግር ያለባቸው ወይም በጣም ከፍተኛ

ሥጋት ያለባቸው የተወሰኑ ገቢ ዕቃዎች ላይ በባለስልጣኑ በየወቅቱ በሚዘጋጀው የመነሻ ዋጋ መሠረት በማነፃፀር የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

2) የመነሻ ዋጋ የሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች በታሪፍ መጽሐፉ ከምዕራፍ 50 እስከ 60፣ በምዕራፍ 64፣ 85፣ 87 ላይ በተዘረዘሩት በቅደም ተከተል የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶች፣ ጫማዎች፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች እና የተሽከርካሪዎችና መለዋወጫዎች እንዲሁም ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ መንገደኞች የሚያስመጧቸው የንግድ መጠን የሌላቸው የግል መገልገያ ጓዝ ዕቃዎች(Passenger's Personal Goods) ላይ ነው፤

3) ዳይሬክቶሬቱ ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጠቃላይ መርህ ጋር በሚጣጣም መንገድ እንዳስፈላጊነቱ የመነሻ ዋጋ የሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች ዝርዝር በመጨመር ወይም በመቀነስ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 22. <u>የዓለማቀፍ ዋጋ መረጃ ምንጮች ስለ መጠቀም</u>

1) በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኙ የገቢ ዕቃዎች ዋጋ ማነፃፀሪያ ካልተገኘ ወይም በሚገኘው መረጃ መሠረት ውሳኔ መስጠት ካልተቻለ ከኢንተርኔት የሚገኘው መረጃ ጨምሮ በዳይሬክቶሬቱ በሚደራጅ ወቅታዊ የአለማቀፍ የዕቃዎች ዋጋ መረጃ በማነፃፀሪያነት በመጠቀም በህጉ ከተደነገገው የዋጋ አተማመን መርህ ጋር በሚጣጣም መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

2) በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ ከሚገኘው ማነፃፀሪያ ውጭ በኢንተርኔት ወይም በሌላ የአለማቀፍ መረጃ በመመርኮዝ የሚሰጠው መስተንግዶ በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ደረጃ ወይም በዳይሬክቶሬቱ ደረጃ አግባብነቱ እየታየ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

3) በቅ/ጽ/ቤቱ ደረጃ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት ስለተሰጠው መስተንግዶ ዝርዝር መረጃዎች ከ15 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ለዳይሬክቶሬቱ መላክ አለበት።

# <u>ምዕራፍ አምስት</u>

# <u>የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክሌራሲዮን</u>

## 23. <u>የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክሌራሲዮን አቀራረብ</u>

1) በአዋጁ አንቀጽ 12 እስከ 18 ስለ ጉምሩክ ዲክለራሲዮን በተደነገገው መሠረት የጉምሩክ ዋጋን በትክክል ለመወሰን እንዲቻል አስመጪው/ወኪሉ የገቢ እቃዎችን አስፈላጊ መረጃዎችን በመሞላትና ለዋጋ አተማመን አስፈላጊ የሆኑ መግለጫ፣ መረጃና ማስረጃዎች ዝርዝር በሙሉ በማያያዝ እና ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን(Valuation Details Decleration [VDD]) ለጉምሩክ ማቅረብ አለበት።

2) ማንኛውም አስመጪ/ወኪል በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት ዲክሌር በማድረግ እቃ ሲያስገባ ከዋናው የጉምሩክ ዲክለራሲዮን (የአሲኩዳ) በተጨማሪ ከዋጋ ትመና ጋር የተገናኙ አስፈላጊ መረጃዎች በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን ውስጥ በትክክል በመሙላትና በማረጋገጥ ለሚመለከተው የባለስልጣኑ ባለሙያ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3) የጉምሩክ ዋጋ መረጃን ወደሲስተሙ የማስገባት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ ለፈጣን አገልግሎት አሰጣጥ ሲባል አስመጪው/ወኪሉ በኤሌክትሪክ፣ ሲስተም መቋረጥ ወይም በሌላ አሳማኝ አጥጋቢ ምክንያት የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን ኢሌክትሮኒክ ሲስተም በማይሰራበት ጊዜ በዋጋ መረጃ ማሳወቂያ ቅጽ/ፎርማት በመጠቀም የዋጋ መረጃን ማቅረብ ይችላል፡፡

## 24. <u>በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክሌራሲዮን ውስጥ መካተት ያለባቸው መረጃዎች</u>

አስመጪው/ወኪሉ የሚከተሉትን መረጃዎችን ጨምሮ በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን በመሞላት ለጉምሩክ ማቅረብ አለበት፡-

1) **ስለ ግብይቱ የሚያስረዱ ዝርዝር መረጃዎች ፡-**

ሀ. አስመጪና ላኪን ጨምሮ በግብይት ውሰጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ስምና ዝርዝር መረጃ

ለ. ስለ ዕቃዎቹ የግብይት ሁኔታ፣

ሐ. በገዢና ሻጭ መካከል ያለውን የግንኙነት ሁኔታና ዓይነት ዝርዝር፣

መ. የኢንቮይሱ ዋጋ፣ የምንዛሪ ዓይነት፣ የንግድ ስምምነት ዓይነት (INCOTERMS) ፣

ሠ. ከዕቃው ጋር በተያያዘ በአስመጪው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብ ወይም በዓይነት የተከፈሉ ክፍያዎች

ረ. ከዕቃው በቀጥታ እና ከዕቃው ጋር ከተያያዙ መብቶች ጋር በተገናኘ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ክፍያ

ሰ. ዕቃውን ለመግዛት የወጡ ሌሎች ወጪዎች፣

ሸ. ከግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ ውጭ አስመጪው በሌሎች የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን በመተመን ለጉምሩክ ካቀረበ የተጠቀመበትን ዘዴ መግለጽ፣

2) **የዕቃውን ዋጋ ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ መግለጫና መረጃዎች፡-**

ሀ. የዕቃው ሙሉ ስም (የንግድ ሥም ወይም ቴክኒካል ስም)፣

ለ. የዕቃውን አምራች ስም፣

ሐ. የዕቃው ተጨማሪ መግለጫ( ለምሳሌ፡- ብራንድ፣ ሞዴል ቁጥር፣ ፓርት ቁጥር፣ መጠን፣ ጉልበት)፣

መ. ዕቃውን የተሠራበት ማተሪያል(ከድብልቅ ማቴሪያል የተሠራ ከሆነ የይዘቱ መቶኛ መጠን)፣

ሠ. የዕቃውን አገልግሎት(ጥቅም) መግለጫ፣

ረ. የመድኃኒት ኬሚካል ስምና ዝርዝር ቴክኒካል መረጃ የሚያሳይ ሰነድ፣

ሰ. የተሽከርካሪ ሥም፣ ዓይነት፣ ሞዴል ቁጥር፣ ምርት ዘመን፣ ሞተር ቁጥር፣ ሻንሲ ቁጥር፣ ሞተር (ሲሊንደር) ጉልበት፣

ሸ. የኤሌክትሮኒክስ፣ የማሽኔሪዎችና መለዋወጫዎች ዝርዝር ማኑዋል እና ቴክኒካል ካታሎግ፣

ቀ. የመለዋወጫ ዕቃዎች ሥም፣ የሚገጠምለት የተሽከርካሪ ዓይነት፣ የአምራች ስም፣ ፓርት ቁጥር፣የእቃው አምራች ፓርት ቁጥር እና የOriginal Equipment Manufacturer's part Number (የኦርጂናል አምራች ፓርት ቁጥር) ፣

በ. የዕቃውን ዋጋ ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መግለጫና መረጃዎች፣

25. <u>ከጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክሌራሲዮን ጋር በአባሪ ስለሚቀርቡ መረጃዎችና ሰነዶች</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 32 እስከ 44 በተደነገገው መሠረት የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን አስመጪው ወይም ወኪሉ ከታች ከአንቀጽ 26 እስከ አንቀጽ 32 የተገለጹትን ዋና ዋና መረጃዎችና ሰነዶችን ጨምሮ ከዲክለራሲዮኑ ጋር እንደ አስፈላጊነቱ በማያያዝ ለጉምሩክ ማቅረብ አለበት።

26. <u>በግብይት ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1) **ግዢ መከናወኑን የሚያሳዩ ሰነዶችና መረጃዎች:-**

ሀ. የዋጋ ሰነድ(የሻጩ ኢንቮይስ)፣

ለ. በግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ አካላት እና ሚናቸው

ሐ. ገቢ ዕቃዎቹ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ከመግባታቸው በፊት ዕቃዎቹን ለመግዛት የተገቡ ውሎችና ሥምምነቶች፣

መ. ከዕቃው ግዢ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች(ለምሳሌ፡ የአስመጪነት ፍቃድ፣ የላኪነት ፈቃድ፣ ፕሮፎርማ ኢንቮይስ፣ የግዢ ስምምነት፣ ፓኪንግ ሊስት፣ የሥሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ የባንክ ፈቃድና ደቢት አድቫይስ፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲና ደረሰኝ፣ የማጓጓዣ ወይም ማስጫኛ ሰነድና ደረሰኝ...)፣

2) **ለዕቃው የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ዋጋ**

ሀ. የሻጩ ኢንቮይስ፣

ለ. ከዕቃው ጋር በተያያዘ በአስመጪው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብ ወይም በዓይነት የተከፈሉ ክፍያዎች የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣

ሐ. ከዕቃው በቀጥታ እና ከዕቃው ጋር ከተያያዙ መብቶች ጋር በተገናኘ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ክፍያን የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣

መ. ዕቃውን ለመግዛት የወጡ ሌሎች ወጪዎች የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣

3) **የኮሚሽን ክፍያ**

ሀ. የውክልና ሥምምነት ሰነድ፣

ለ. የኮሚሽን ክፍያ ዓይነት የሚገልጽ ሰነድ፣

ሐ. የሻጩ ወይም የኮሚሽን ክፍያ ኢንቮይስ፣

***4) የማሸጊያ ወጪ***

*ሀ. ዕቃውን ለማሸግ የወጣ የማቴሪያሎችም ሆነ የጉልበት ዓይነትና ወጪ፣*

*ለ. ዕቃውን የማሸግ ሥራው የተከናወነበት ቦታ ወይም አገር፣*

*ሐ. ዕቃውን የማሸግ ሥራው ያከናወነው አካል፣*

5) ***ዕቃው እስከተጫነበት ወደብ ድረስ የተከፈለ ትራንስፖርትና ኢንሹራንስ ወጪ***

ሀ. ዕቃው የተላከበት (Place of export) ሀገርና ኮንቴነራይዝ የተደረገበት ቦታ ማስረጃ፣

ለ. ዕቃው በተላከበት ሀገር ወደብ እስኪደረስ የወጣ የማጓጓዣ ወጪ ማስረጃ፣

ሐ. በዕቃው ግብይት ወቅት ጥቅም ላይ የዋለ ዓለምአቀፍ የንግድ ሥያሜ (INCOTERMS)

6) ***ዕቃው ከተጫነበት ወደብ እስከ መጀመሪያ የኢትዮጵያ መግቢያ ድረስ የተከፈለ የውጭ ሀገር የማጓጉዣና የኢንሹራንስ ወጪ***

ሀ. የማጓጓዣ እና የኢንሹራንስ ሥምምነቱን ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ፣

ለ. ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪዎች ማስረጃ፣

7) **በአስመጪው ለላኪው የቀረቡ ግብዓቶችና አገልግሎቶች**

ሀ. ዕቃውን ለማግኘት ወይም ለማምረት በገዢው በቀጥታ ወይም በገዢው ሥም በሦስተኛ ወገን በኩል ለአምራቹም ሆነ ለላኪው የቀረቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር፣

ለ. ከላይ የተጠቀሱት ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማምረቻ ወጪ ወይም የግዢ ዋጋ እና የማድረሻ ወጪ የሚያሳይ ማስረጃ፣

8) **የሮያሊቲና ፈቃድ ክፍያዎች**

ሀ. በዕቃው ግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን አካላት ሚናና ግንኙነት የሚያስረዳ መግለጫ፣

ለ. የሮያሊቲና ፈቃድ ሥምምነት ሰነድ፣

ሐ. የሽያጭ ሥምምነት ሰነድ፣

መ. ከዕቃው ገዢ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች፣

9) ***መልሶ ከመሸጥ ከሚገኘው ገቢ ላይ የሚከፈሉ ክፍያዎች***

ሀ. የሽያጭ ሥምምነት ሰነድ፣

ለ. ገዢው ዕቃው መልሶ በመሸጥ፣ በሌላ በማስተላለፍ ወይም በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ ለሻጩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚከፈሉ ክፍያዎች የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣

ሐ. ከዕቃው ገዢ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች፣

10) ***ዕቃው ሀገር ውሰጥ ከገባ በኋላ የተሰጠ ወይም የሚሰጥ የቴክኒክ ድጋፍ***

ሀ. የዕቃዎች ወይም የአገልገሎቶች ግዢ ውል ሰነድ፣

ለ. ክፍያዎቹ ዕቃዎቹ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለወጡ ወጪዎች የተከፈሉ መሆናቸውን የሚያሳይ መገለጫ፣

ሐ. የተደረገው/የሚደረገው ድጋፍ ዓይነትና ወጪ መጠን ማስረጃ፣

መ. ወጪዎቹ ለዕቃው በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውሰጥ መካተታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣

*11) ዕቃው ሀገር ውሰጥ ከገባ በኋላ የተከፈሉ የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪዎች*

ሀ. ዕቃዎች ሀገር ውሰጥ ከገቡ በኋላ የወጣ የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪ መኖሩን የሚያሳይ መግለጫ፣

ለ. የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪው መጠን፣

ሐ. የአገልግሎቱ ባህሪና ሁኔታ፣

መ. ወጪው በዕቃው በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ መካተቱን ወይም አለመካተቱን የሚያሳይ ማስረጃ፣

12) **ተቀናሽ የፋይናንስ ወጪዎች፤**

ሀ. ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡት እቃዎች ግዥ ጋር በተያያዘ በገዢው የተከፈለውን የብድር ወይም የፋይናንስ ወለድ ክፍያና የክፍያ ስምምነት ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ፣

ለ. ክፍያውን ዘግይቶ እንዲፈፀም የሚያስችሉ ሥምምነቶች የሚያስረዳ ሰነድ፣

13) **ግንኙነት(ዝምድና) ያላቸው አካላት፣**

ሀ. በገዢና ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት ሁኔታና ዓይነት፣

ለ. በገዢና ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት በዕቃው ግብይት ዋጋ ላይ ያለው ተፅዕኖ የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ፣

ሐ. የኮርፖሬቱ(ድርጅቱ) ዝርዝር ፕሮፋይልና የዋጋ ፖሊሲ የሚያሳይ ሰነድ፣

መ. የገዢውን የማከፋፈል ወይም የኤጀንት(ብቸኛ ወኪል) መብት ስምምነት የሚያሳይ ሰነድ፣

ሠ. የዕቃው የሽያጭ የውል ሰነድ እና የሻጩ ኢንቮይስ፣

ረ. በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት በሌላቸው ገዥና ሻጭ መካከል የተከናወነ ሽያጭ (ወደ ኢትዮጵያ የተላኩ) አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣

ሰ. ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ሰነዶች፣

27. <u>የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበትን ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣
2) ከዕቃው በፊት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎችን በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡ ነጠላ ዋጋ (Unit Price) የሚያሳይ ማስረጃ፣
3) በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎች ማስረጃ፣
4) የዕቃውን የአምራች የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር መረጃ(Price List) የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ፣

28. <u>የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበት ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣
2) ከዕቃው በፊት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተመሳሳይ ዕቃዎችን በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡ ነጠላ ዋጋ (Unit Price) የሚያሳይ ማስረጃ፣
3) በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ተመሳሳይ ዕቃዎች ማስረጃ፣
4) የዕቃውን የአምራች የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር መረጃ (Price List) የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ፣

29. <u>ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ ዋጋን ለመተመን መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበትን ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣
2) በሻጩ (አስመጪው) እና በገዢው(አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ነጋዴ) መካከል ያለው የዝምድና ሁኔታ እና በእቃው የሀገር ውስጥ መሸጫ ዋጋ ላይ ያለው ተጽእኖ የሚያስረዳ ማስረጃ ፣
3) የሽያጩ ሁኔታ የሚያስረዱ መረጃዎችና ማስረጃዎች፣
4) የሻጩ (አስመጪው) ዕቃዎችን የሚሸጥበት ዋጋ ዝርዝር ማስረጃ፣
5) የሽያጭ የውል ሰነድ ወይም ኢንቮይስ እና ክፍያ የተፈጸመበት ማስረጃ፣

30. <u>የዕቃውን ጉምሩክ ዋጋ በወደ ኋላ ማስላት ዘዴ ለማስላት የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች</u>፡-

1) የመሸጫ ዋጋ፣ የመሸጫ ወጪ እና የመሸጫ ትርፍ፣
2) ሌሎች ከዕቃው ጋር በተያያዘ በሀገር ውሰጥ የወጡ ወጪዎችና ክፍያዎች ዝርዝር፣

3) ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ከመሸጡ በፊት የተከናወነ ቀጣይ የምርት ሂደት ካለ፤ ያስከተለው ተጨማሪ እሴት መጠን የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣
4) ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች የሚከፈሉ የቀረጥና ታክስ መጠን፣
5) የዕቃውን የንግድ ዘርፉን አማካይ የኮሚሽን፣ የወጪዎችና የትርፍ ምጣኔ የሚያሳይ ማስረጃ፣
6) የዕቃውን የንግድ ዘርፉን አማካይ የማጓጓዣ፣የኢንሹራንስና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች ምጣኔ የሚያሳይ ማስረጃ፣

31. <u>በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበት ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣
2) ዕቃዎቹ በላኪው የተመረቱና የተላኩ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣
3) በላኪው ሀገር ዕቃዎቹን ለማምረት የወጣውን የማምረቻ ወይም የማዘጋጃ ወጪ የሚያሳይ ማስረጃ፣
4) በላኪው ሀገር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ ወይም የእቃውን ንግድ ዘርፉን አብዛኛውን ጊዜ ያለው (የተለመደ ወይም አማካይ) የመሸጫ፣ የማሸጊያና ሌሎች ወጪዎች እና የትርፍ መጠን ማስረጃ፣
5) ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ማስረጃ፣
6) ለዕቃዎቹ የወጣ ሌሎች ክፍያዎችና ወጪዎች የሚያሳይ ማስረጃ፣

32. <u>ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ዋጋን መወሰን መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች፣</u>

1) በዚህ ዘዴ መሠረት የዕቃውን ዋጋን መተመን ትክክል የሚሆንበት ምክንያት የሚያሳይ ማስረጃ፣
2) በዚህ ዘዴ መሠረት የዕቃውን ዋጋን ለመተመን የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ሰነዶች፣

## ክፍል ሶስት

## የጉምሩክ ዋጋ ትመና የሚያከናውኑ አካላት ወይም ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

## ምዕራፍ አንድ

## የዳይሬክቶሬቱ፣ የሥራ ክፍሎች እና ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

33. የዳይሬክቶሬቱ ተግባርና ኃላፊነት

ዳይሬክቶሬቱ በባለሥልጣኑ ከተሰጠው ሌሎች የሥራ ኃላፊነትና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናል፡-

1) የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋትን ማልማት፣ ማሻሻልና ማስተዳደር፣

2) በባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ የዋጋ መረጃዎችን እና ከሌሎች በአለማአቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካላቸው የዋጋ መረጃ ምንጮች የዋጋ መረጃ መሰብሰብ እና መተንተን፤ የተተነተነውን የዋጋ መረጃ ለአጠቃቀም በሚመች መልኩ ማዘጋጀት ወይም ማደራጀት፤በዋጋ መረጃ ቋቱ የሚገኝ መረጃን ተገቢው ማስተካከያ ማድረግ እና በየጊዜው የዋጋ መረጃ ቋቱ ወቅታዊ በማድረግ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተደራሽ እንዲሆን እና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

3) ሁሉም የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ እና ተመሳሳይ የዋጋ አተማመን ሥርዓት እየተከተሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በየጊዜው አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

4) ከቅ/ጽ/ቤቶች እና ከሌሎች ክፍሎች በዋጋ ትመና የአሠራር ሥርዓት ዙርያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በጥናት ላይ የተመሠረተ ምላሽ መስጠት፤

5) ዳይሬክቶሬቱ ከሚያገኘው መረጃዎችና ከሚቀርብለት ሪፖርቶች በመነሳት ሳይሰበሰብ የቀረ ቀረጥና ታክስ ካለ አጣርቶ በሚመለከተው ቅ/ጽ/ቤት የድህረ እቃ አወጣጥ የስራ ሂደት/ክፍል አማካይነት እንዲሰበስብ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ፣

6) በዋጋ አተማመን የአሰራር ስርአት ዙርያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለተቋሙ ሰራተኞችና ለሚመለከታቸው አካላት መስጠት፣

7) ባለስልጣኑን ወክሎ በዋጋ አተማመን ዙሪያ ከተጓዳኝ መ/ቤቶች እና ከሌሎች ሀገራትና የአለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግኑኝነት በመፍጠርና በማዳበር አስፈላጊ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር በአገራችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

8) በዋጋ አተማመን ዙሪያ የአሰራር ማኑዋል ማዘጋጀት ፤በዋጋ አተማመን ዙሪያ አዋጅ፣መመሪያው እንዲሁም የአሰራር ማኑዋሉ በባለስልጣኑ ተግባራዊ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ፣

9) ሌሎች ከዋጋ ትመና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት መፈጸም፡፡

34. <u>የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በባለሥልጣኑ ከተሰጠው ሌሎች የሥራ ኃላፊነትና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናል፡-

1) የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋት (ECVS) እና ኤልክትሮኒክ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ማቅረቢያ ዲክሌራሲዮን (VDD) በተመለከተ፣
   ሀ. ዘመናዊ፣ ጥራት ያለው እና ለአጠቃቀም ቀላል እንዲሆን በየጊዜው በመፈተሽ ተገቢው ማሻሻያ ያደርጋል፣
   ለ. አገልግሎቱ ሳይቋረጥ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ያደርጋል፣
   ሐ. የአጠቃቀሙን ሁኔታ በመገምገም ከዳይክቶሬቱ ጋር በመወያየት አስፈላጊው ማሻሻያ ያደርጋል፣
2) የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋትን በተመለከተ በሚወጣው ዝርዝር የአፈጻፀም መመሪያ መሠረት በሚመለከተው የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ወይም በዳይሬክቶሬቱ ፈቃድ ያገኙ የሚመለከታቸው ሠራተኞችን በመለየት፣ የመጠቀሚያ መለያና የይለፍ ቃል (ፓስዎርድ) መስጠትና መሰረዝ፣ አስፈላጊው የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት እና መቆጣጠር፣

3) በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋት አጠቃቀም ዙርያ ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመተባበር ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና ቅ/ጽ/ቤቶች ስልጠናና አስፈላጊው ድጋፍ መስጠት፣

4) ከዳይሬክቶሬቱ ጋር አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ ሥርአት በመዘርጋት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

5) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመረጃ ቋቱ የአጠቃቀም ሪፖርቶችን በማውጣት ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች መስጠት
6) ከብሔራዊ ባንክ የሚላከውን ወቅታዊ የገንዘብ ምንዛሪ ልክ በመቀበል በአሲኩዳ ሲስተም ውስጥ በወቅቱ በማስገባት በባለስልጣኑ ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

35. <u>የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ሃላፊነት</u>

ሁሉም የሚመለከታቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ሌሎች በባለሥልጣኑ የተሰጣቸውን የሥራ ኃላፊነትና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናሉ፡-

1) በባለሥልጣኑ የሚወጡ የዋጋ አተማመን መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች እና የአሰራር ሥርዓቶች እንዲሁም የፕሮሲጀር ማንዋሎች  በትክክል ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ

2) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የዋጋ መረጃ ዳታቤዝ በወጥነት እና በትክክል ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

3) ለዋጋ መረጃ ዳታቤዝ በግብአት የሚገለግሉ መረጃዎች እና ከዋጋ መረጃ ዳታቤዝ ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶችና መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ በጥራትና በአግባቡ እንዲመዘገቡ/እንዲደራጁ/ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በየጊዜው ለዳይሬክቶሬቱ ማስተላለፍ፣

4) በቅ/ጽ/ቤቱ ደረጃ ለሚቀርቡ የዋጋ እና ከዋጋ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች በቅ/ጽ/ቤቱ የዋጋ ትመና ቡድን በኩል አግባብነት ያላቸውን የዋጋ መረጃ ምንጮች በማገናዘብ ወጥነት ባለው መልኩ ምላሽ እንዲሰጣቸው ማድረግ፣

5) በቅ/ጽ/ቤቱ ለሚገኝ የዋጋ ትመና ቡድን የሚቀርቡ ከዋጋ አተማመን አሠራር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ከቅ/ጽ/ቤቱ አቅም በላይ ሲሆኑ ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመነጋገር ጥያቄውን ላቀረበው አካል ምላሽ መስጠት፣

6) በቅ/ጽ/ቤቱ ለሚገኝ የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ የሥራ ሂደት በተለያየ ጊዜ ለሚቀርቡ የዋጋ እና ከዋጋ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ቡድኑ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች ለዳይሬክቶሬቱና ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ፣

7) በቀጥታ በኔትዎርክ ያልተገናኙ የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ተቀባይነት ያገኙ ዋጋዎችን በማጠናቀርና በኤክሴል ፎርማት በማዘጋጀት በየወሩ መጨረሻ ለዳይሬክቶሬቱ መላክ፤

8) በቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኝ የዋጋ ትመና ቡድን ባስተላለፋቸው ውሳኔዎች ላይ ጥያቄዎች ሲቀርቡ እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከተው አካላት ማብራሪያ መስጠት፣

9) በባለሥልጣኑ ደረጃ በሚዘጋጀው ዝርዝር የአፈጻፀም ማኑዋል መሠረት በአግባቡ መሥራት፣

10) ሌሎች በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ መፈፀም ያለባቸው ዋጋ ትመናን የተመለከቱ ሥራዎች ማከናወን ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለ የጉምሩክ ኦፊሰሮች ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት

### 36. የጉምሩክ ኦፊሰሮች የዋጋ ማጣራት ስልጣን

1) የሰነድ ማረካከቢያና ማረጋገጫ ኦፊሰር (የፌስቬት ኦፊሰር) አንድ ዲክለራሲዮን ዲክለር ተደርጎ ለባለስልጣኑ ሲቀርብ የቀረበውን ዲክለራሲዮን የተሟላ ሰነድ እና ትክክል መሆኑን መረጃውን ከአሲኩዳ እና ቪ.ዲ.ዲ ከገባው መረጃ አንጻር በማረጋገጥ ይረከባል፤ዲክለራሲዮኑ በባለስልጣኑ ካለው የስጋት ደረጃ አንጻር አጣርቶ ለቀጣይ ስራ ለሚመለከተው ኦፊሰር ያስተላልፋል፡፡

2) በቅ/ጽ/ቤቱ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በየደረጃው በማንኛውም ጊዜ የዋጋ ማጣራት ሥራዎች የሚከናወን ይሆናል፡፡

3) የጉምሩክ ፎርማሊቲ አሟልቶ ዲክሌር በተደረገውና በአስመጪው/ወኪሉ በቀረበው ዲክለራሲዮን ላይ ተዘርዝረው የሚቀርቡ እቃዎች ዋጋ የሚጣራውና ውሳኔ የሚሰጠው በዚህ አንቀጽ መሠረት ዲክሌር በተደረገው የዋጋ መጠን እና የሥራ ኃላፊነት ደረጃ መሠረት ይሆናል፣

4) በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የጉምሩክ ኦፊሰሮች የሚከተሉት የማጣራት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡-

   ሀ. በአንድ ዲክለራሲዮን ውስጥ ከብር500,000 (አምስት መቶ ሺ) ያልበለጠ የፎብ ዋጋ ያላቸው ገቢ ዕቃዎች በሠነድ ምርመራ ኦፊሰር ወይም ሌላ የሚመለከተው ኦፊሰር የሚጣሩና ውሳኔ የሚሰጣቸው ይሆናል፤

   ለ. በአንድ ዲክለራሲዮን ውስጥ ከብር500,000 (አምስት መቶ ሺ) በላይ የፎብ ዋጋ ያላቸው ገቢ ዕቃዎች በሠነድ ምርመራ ከፍተኛ ኦፊሰር ወይም ሌላ የሚመለከተው ከፍተኛ ኦፊሰር የሚጣሩና ውሳኔ የሚሰጣቸው ይሆናል፤

5) ከላይ በንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 በተገለጸው መሠረት በቅደም ተከተል በሰነድ ምርምራ ኦፊሰሮች ውሳኔ ሲሰጥ ከዋጋ ትመና እና ታሪፍ ምደባ ጋር ተያይዞ የሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ከዋጋ ትመና ታሪፍ ምደባ ሥራ ሂደት አስፈላጊው ድጋፍ ይገኛሉ፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) በተደነገገው መሠረት ለአፈፃፀም ሲባል በተወሰኑ የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ውስጥ መዋቅሩ ወይም የሥራ መደቡ ከሌለ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ

አስኪያጅ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም አግባብነት ያለው የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ለኦፕሬሽን ዲዛይን ፕሮግራምና ልማት ሥራዎች ዘርፍ ያሳውቃል፡፡

**37. <u>የጉምሩክ ኦፊሰሮች ዋጋ የመወሰን ስልጣን</u>**

1) የሚመለከታቸው የጉምሩክ ኦፊሰሮች አስመጪው/ወኪሉ ከዋጋ ትመና ጋር በተያያዘ ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ ወይም የዋጋ ልዩነት ሲገኝ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ዋጋ የማጣራት፣የማስተካከል ወይም ተገቢውን ውሳኔ የመወስን ስልጣን ተሰጥቷቸል፡፡

    ሀ. የልዩነት አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ኦፊሰር በአንድ ዲክለራሲዮን የልዩነት ዋጋቸው ከብር 250000(ሁለት መቶ ሀምሳ ሺ) ያልበለጠ የፎብ ዋጋ ያላቸው ገቢ እቃዎች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

    ለ. የልዩነት አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ከፍተኛ ኦፊሰር በአንድ ዲክለራሲዮን የልዩነት ዋጋቸው ከብር 250000(ሁለት መቶ አምሳ ሺ) እስከ 500000(አምስት መቶ ሺ) ድረስ ያልበለጠ የፎብ ዋጋ ያላቸው ገቢ እቃዎች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

    ሐ. የልዩነት አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቡድን አስተባባሪ በአንድ ዲክለራሲዮን የልዩነት ዋጋቸው ከብር 500000(አምስት መቶ ሺ) በላይ የፎብ ዋጋ ያላቸው ገቢ እቃዎች እና ጉዳያቸው ከበድ ያሉ እቃዎችን ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

2) በተሰጠው ውሳኔ ላይ የሚመለከተው ኦፊሰር ወይም የስራ ክፍል ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊው ማብራሪያና ማስረጃ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ሃላፊነት አለበት፡፡

3) በእቃ አወጣጥ ቡድን የዋጋ ልዩነት ከተገኘ ወይም በቡድኑ ውሳኔ መስጠት ካልተቻለ ሪፖርቱና አስፈላጊው ሰነድና መረጃ በማያያዝ ለጉምሩክ ስነ-ስርአት ደንብ መተላለፍ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቡድን ያስተላልፋል፡፡

4) የጉምሩክ ስነ-ስርአት ደንብ መተላለፍ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቡድን የቀረበለትን የዋጋ ጥያቄ በቡድኑ ውሳኔ መስጠት ካልተቻለ ሪፖርቱና አስፈላጊው ሰነድና መረጃ በማያያዝ ጥያቄውን ለዋጋ ትመና ቡድን በማቅረብና ከቡድኑ በሚሰጠው አስተያየት (ውሳኔ) ከተቀበለ በኋላ ተገቢውን ማስተካከያና ውሳኔ ማስተላለፍና ገቢ መሰብሰብ አለበት፡፡

5) የቅ/ጽ/ቤቱ የዋጋ ትመና ቡድን አስፈላጊውን መረጃዎችን በማደራጀትና አስተያየቱን በመስጠት ለሚመለከታቸው አካለት ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት ለአፈጻጸም ሲባል በተወሰኑ የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ውስጥ መዋቅሩ ወይም የስራ መደቡ ከሌለ የሚመለከተው የቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር በማጣጣም አግባብነት ያለው የአሰራር ስርአት በመዘርጋት በወቅቱ ለዳይሬክቶሬቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

38. <u>የጉምሩክ ኦፊሰር ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የሚመለከተው የጉምሩክ ኦፊሰር በአዋጅ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የዕቃውን ዋጋ የመተመን እና ቀረጥና ታክስ የማስላት ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡

2) የጉምሩክ ኦፊሰር በቀረበው ዋጋ ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ካደረበት የዋጋ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሰነዶችን ሁሉ አሟጦ በመጠቀም ውሳኔ መስጠት እንዲችል ከአስመጪው ወይም ከወኪሉ ተጨማሪ መረጃና ሰነድ መጠየቅ አለበት ፡፡

3) አስመጪው/ወኪሉ በጉምሩክ ኦፊሰር የተጠየቀውን ተጨማሪ መረጃና ሰነድ ማቅረብ ካልቻለ ወይም ምላሽ ካልሰጠ ኦፊሰሩ የእቃዎቹን ዋጋ አስመጪው/ወኪሉ ባሳወቀው መሠረት መተመን እንደማይቻል በመግለጽ ለአስመጪው/ወኪሉ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

39. <u>የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ስለ ማድረግ</u>

1) በአዋጁ ውስጥ ስለ ድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ከተደነገገው አንጻር በሚደግፍና በሚጣጣም መልኩ በቅ/ጽ/ቤት እና በዋ/መ/ቤት ደረጃ በሚቋቋመው የክለሳ ኮሚቴ በኩል የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ይደረጋል፡፡

2) የቅ/ጽ/ቤት የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ከእቃ አወጣጥ ቡድን፣ ከልዩነት አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቡድን፣ከዋጋ ትመና ቡድን እና ከድህረ-እቃ አወጣጥ የሥራ ሂደት የተውጣጡ ባለሞያዎች ይኖሩታል፡፡

3) የቅ/ጽ/ቤት የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴ በሚደርሰው መረጃ ወይም ዋጋውን ካጣራው ኦፊሰር ቢያንስ በአንድ ደረጃ የሚበልጥ የበላይ ሀላፊ በቀረበ አስተያየት ወይም ከዋ/መ/ቤት የዋጋ ማጣራት ክለሳ ኮሚቴ  በቀረበ አስተያየት/መረጃ/ መነሻነት በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ በሚገኙ የጉምሩክ ኦፊሰሮች ወይም ባለሞያዎች የተሰጠው የዋጋ ውሳኔ በአዋጅ፣ በደንብ፣ በመመሪያና በአሠራር መሰረት በአግባቡ ስለመከናወኑ በድጋሚ ክለሳ ያደርጋል፡፡

4) የቅ/ጽ/ቤት የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴ የሚያስተላልፏቸው የዋጋ ውሳኔዎች በሙሉ ወደ ዋናው መ/ቤት የዋጋ ክለሳ ኮሚቴ መላክ ይኖርባቸዋል፡፡

5) የዋናው መ/ቤት የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለኦፕሬሽን ዲዛይንና ፕሮግራም ልማት ዘርፍ ሆኖ ከዳይሬክቶሬቱ፣ ከድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ከሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል፡፡

6) ዳይሬክቶሬቱ ከዋናው መ/ቤት የዋጋ ክለሳ ኮሚቴ የሚመጡለትን ሰነዶች በመመርመርና እንዲሁም በማደራጀት ለዚሁ ኮሚቴ እገዛ ያደርጋል፡፡

7) በዚህ አንቀጽ መሠረት በዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴዎች በተገኙት ግኝቶች መሠረት ቀሪ ሂሳብ ካለ ለሚመለከተው የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ክፍል በማስተላለፍ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡

8) የዋጋ ክለሳ ሥራ የዕቃው ዲክሌራሲዮን የመጀመሪያ ማጣራት ከተደረገበት እለት አንስቶ እስከ 10(አሥር) አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>የአስመጪው ግዴታዎች እና መብት</u>

### 40. <u>የአስመጪው ወይም ወኪሉ ግዴታዎች</u>

1) አስመጪው ወይም ወኪሉ በጉምሩክ አዋጅና በዚህ በመመሪያ በተደነገገው መሠረት የጉምሩክ ዲክለራሲዮን፣ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክሌራሲዮን እና ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም አስፈላጊ ከሆኑ ደጋፊ ሰነዶች ጋር በማያያዝ ለጉምሩክ ማቅረብ አለበት፡፡

2) አስመጪው ወይም ወኪሉ የዕቃው የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን በሚያቀርብበት ጊዜ፡-

   ሀ. የተሟላና ትክክለኛ የሆነ ከገቢ ዕቃዎቹ ዋጋ አተማመን ጋር ግንኙነት ያላቸው ዝርዝር መረጃዎችና ሰነዶች ማቅረብ አለበት፣

   ለ. በባለሥልጣኑ በኩል በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚዘጋጁ ቅጾች ወይም ሰነዶች ላይ መረጃ በአግባቡ በመሙላት ማቅረብ አለበት፡፡

   ሐ. ለባለሥልጣኑ በሚያቀርባቸው ዲክሌራሲዮን፣ መረጃዎች እና ደጋፊ ሰነዶች ትክክለኛነት ኂላፊነት ያለበት ሲሆን፤ አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂና ኂለፊነት ያለበት መሆኑን በፊርማው በማረጋገጥ ለጉምሩክ ማቅረብ አለበት፡፡

### 41. <u>የአስመጪው ወይም ወኪሉ መብት</u>

1) አስመጪው በባለሥልጣኑ ወይም በጉምሩክ ኦፊሰር የተሰጠው ውሳኔ በጽሁፍ የማወቅ መብት አለው፡፡

2) በባለስልጣኑ መ/ቤት በሚመለከተው የጉምሩክ ኦፊሰር በሚወስነው የቀረጥና ታክስ መጠን አስመጪው ዋስትና በማስያዝ ዕቃውን ማስለቀቅ ይችላል፡፡

3) አስመጪው ዋስትና በማስያዝ ዕቃውን ማስለቀቅ የሚችልባቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው፡፡

ሀ. ለዋጋ አተማመን የሚያስፈልጉ ሰነዶችና መረጃዎች በበቂ ምክንያት ያልተሟሉ ሲሆንና እነዚህ ለማሟላት ተጨማሪ ጊዜ ሲያስፈልግ፣

ለ. የእቃዎችን ዋጋ በአጭር ጊዜ በማጣራት ተገቢው ውሳኔ ማስተላለፍ በማይቻልበት ጊዜ፣

4) በባለስልጣኑ በተሰጠው የዋጋ ውሳኔ ላይ ያልተስማማ አስመጪ በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች ውስጥ በተደነገገው መሠረት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ሌሎች ድንጋጌዎች፡

**42. የገንዘብ ምንዛሪ**

የገንዘብ ምንዛሪን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 44 በተደነገገው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**43. ልዩ የዋጋ መስተንግዶ ሁኔታ**

1. ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ የተደነገገው ቢኖርም በሥጋት ሥራ አመራር አሠራር መሠረት ተጣርቶ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያለውን ዕቃ ዋጋው በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ ከተያዘው ዋጋ ጋር ያለው ልዩነት ከ10 በመቶ የበለጠ ቢሆንም ለሚመለከተው የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት በመምራት ቀጣይ የማጣራት ሂደት እና ቀሪ ሂሳብ ካለም የመጠየቅ ሂደት እንደተጠበቀ ሆኖ አስመጪው ባቀረበው ሰነድ (በኢንቮይስ ዋጋ) መሠረት ሊያስተናገድ ይችላል፡፡

2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ከታች ከፊደል ሀ እስከ ሐ ድረስ የተመለከቱትን እና ሌሎች ተመሳሳይ አስመጪዎችን ጨምሮ እንደ አስፈላጊነቱ ሊያስተናግድ ይችላል፡፡

ሀ. የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች፣

ለ. አምራች ድርጅቶች ወይም የሁለተኛ ታሪፍ መደብ ተጠቃሚዎች ለግብአት የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎች ሲያመጡ፣

ሐ. በባለሥልጣኑ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ/AEO/ አስመጪዎች፣

3. ቅ/ጽ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 በተደነገገው መሠረት የሰጠውን መስተንግዶ የተመለከተ ዝርዝር ሪፖርት በማዘጋጀት በየ15 ቀኑ ለዳይሬክቶሬቱ እና ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ማስተላለፍ አለበት፡፡

## 44. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1) የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት ፣አዘገጃጀት ፣ስርጭትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 10/1996፣
2) የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት አዘገጃጀት ስርጭትና አጠቃቀም አስመልክቶ የወጣውን መመሪያ ለማስፈጸም የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/1996፣ እና
3) ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እና እቃዎች የዋጋ አተማመን እና የቀረጥ እና የታክስ ስሌት መወሰኛ መመሪያ ቁጥር 6/1996 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡
4) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጋጩ ወይም የማይስማሙ ሌሎች መመሪያዎችና ሰርኩላሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 45. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1) ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በእንጥልጥል የነበሩ እና በባለሥልጣኑ መ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በነባሩ መመሪያ መሰረት ይሰተናገዳሉ፡፡
2) አዲሱ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት በሚፈለገው ደረጃ ሙሉ ትግበራው እስኪጀምር ድረስ ከዚህ በፊት ይሰራበት የነበረው ነባሩ የዋጋ መረጃ ዳታቤዝ (የሲዲ ዋጋ መረጃ ዳታቤዝ) እንደ አስፈላጊነቱ ለተወሰነ ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

## 46. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ -------------ቀን 2006 ዓ.ም

በከር ሻሌ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር